ምን ያሳስበናል?

የዚህችን ዓለም ትከከለኛ ምንነት ማወቅ ትልቅ ፋይዳ አለው። በትከከል ሰናውቃት ሳናጋንንም ሆነ ሳናናንቅ በሷነቷ ልከ እንኖራለን። የእንድን ነገር ትከከለኛ ዋጋ ማወቅ ያረጋጋል፤ ሚዛናዊ ያደርጋል፣ በእርጋታ ለመኖር ያግዛል። የተሳሳተ አረዳድ ግን ወደተሳሳተ ግንዛቤ ያደርሳል። ለተሳሳተ ውሳኔም ይዳርጋል። ዱንያን ስንገነዘባት ለሷ ያለን ከልከ ያለፈ ጉጉትም ይቀንሳል።

ከሁሉ በፊት "ይህች ምድር ጊዜያዊ ናት" የሚለውን እውነት በጥልቀት ልናውቀው ይገባል። እሷ ቋሚ ወደሆነው ወደዚያኛው ዓለም መሸጋገሪያ እንጂ ሌላ አይደለችም። ከጊዜያዊነቷ ባሻገር ደግሞ የፈተና እና የውጣ ውረድ አገር ተደርጋ የተፈጠረች መሆኑንና ልናውቅ ይገባል። የሰው ልጅም በሷ ውስጥ የተደረገው እንዲለፋና ከጥሩ ውጤት እንዲደርስ ነው። ይህ ዕጣፈንታው ነው። ምድርን አስኪለቅ ድረስ ይለፋል፣ አብዝቶም ይደከማል...።

አላህ (ሱ.ወ.) ወላጆቻችንን አባታችንና እናታችንን አደምና ሀዋ ጀነት ውስጥ አያሉ ከሸይጣን ተንኮል ሲያስጠነቅቃቸውና ሲመክራቸው "ከጀነት እንዳያስወጣችሁና ልፋት እንዳያገኛችሁ" ነበር ያላቸው። "ልፋት እንዳያገኛችሁ" የተባሉት ምድር ላይ የሚያጋጥማቸውን የመከራና የድካም ሕይወት ለማመላከት ነው። በርግጥም ከጀነት ሲወጡ ምድር ላይ መከራ ጠበቃቸው። ስለዚህ መከራ የምንኖርባት ምድር መገለጫ ነው ማለት ነው። በመሆኑም በሚደርስብን ማንኛውንም ዓይነት ችግር ልንገረምም ሆነ ልንደነግጥ አይገባም። ባይሆን ፅናት፣ ትዕግስትና ብርታትን መሰነቅ ነው የሚያስፈልገው።

ምድር ላይ እስከኖረ ድረስ የሰውን ልጅ አታስብ፣ አትጨነቅ፣ አትዘን፣ አትብሰልሰል... ማለት ይከብዳል። በርግጥ የሰውን ልጅ የሚያሳስቡት ነገሮች ብዙ ናቸው። በዱንያ ላይ መገኘት በራሱ ትልቅ ሃላፊነት ነው። ለዚህም ነው ብዙዎች ራሳቸውን አብዝተው የሚጠሉት። ባልተፈጠርኩ፣ ወደዚህች ምድር ባልመጣሁ የሚሉት። ግና ዱንያን ገና አላህ ሲፈጥራት የጭንቅና የሃላፊነት አገር አድርጎ ነው። ግና በትከከል እሷን ስንገነዘብ ግን ሃላፊነት ጭንቀቱም ይወገድልናል። አዎ የዱንያን ምንነት እንወቅ። አውቀንም በልኳ እንኑራት ...

አሰቲ ምን አሳሰበን? ....

መከራ የዚህች ምድር ባህሪ መሆኑን እሷንም ሆነ እኛን የፈጠረ ጌታ አላህ (ሱ.ወ.) አስቀድሞ ነግሮናል። ስለዚህም መከራ የወረደብን ወደ ምድር የመጣን ቀን ነው ማለት ነው። ችግር፣ በሽታ፣ ድካም፣ ውድቀት፣ ድህነት... ባህሪዋ ነው። እሷ ጎዶሎ ሆና ነው የተፈጠረችው፤ ፍፁም አይደለችም። ድፍርስ ናት፤ ንፁህ አይደለችም። ሁከት የበዛባት ናት፤ ሰላማዊና ፀጥተኛ አይደለችም። የዚህ ዓይነት ባህሪ ካላት ዓለም የተለየ ነገር እንድትሠጠን መጠበቅ የለብንም። - የዱንያ ምንነት።

ምን ያስጨንቀናል? ...

የሰው ልጅ ሆኖ ከዚህች ምድር መከራ ያልቀመሰ ማንም የለም። ይብዛም ይነስ ሁሉም ከችግር ፅዋዋ ተጎንጭቷል። በልዩነት እኛን ብቻ መርጦ እኛ ላይ ብቻ የወረደ መከራ የለም። "የኔ ይብሳል፤ የኔ ይለያል" የምትለዋ ቃል ሁሉም ቤት አለች። ከአላህ (ሱ.ወ.) ምርጥ ነቢያት፣ ከደጋግ ባሮቹ ጀምሮ እስከ ተራ ሰዎች ሁሉ በዱንያ አለንጋ ተገርፈዋል። ነቢያት ሁሉ አንድም ሳይቀሩ አደም፣ ኑሕ፣ ዩኑስ፣ ዩሱፍ፣ ዘከርያ፣ የሕያ፣ ሙሳ፣ ዒሳ... ሁሉም በተለያዩ የችግር ዓይነቶች ውስጥ አልፈዋል። በጀነት የተመሰከረላቸው ምርጥ ሰዎች ሳይቀር ቀጥ ባለ መስመር ተጉዘው አይደለም ጀነት የገቡት። በርካታ ውጣውረዶችን አይተዋል። ይህን ባህሪዋን ካወቅን እሷ በምታደርግብን ጫና ፈጽሞ ልንፍረከረክም ሆነ ልንንበረከክ አይገባም። እናም ፈታ እንበል ምን ያስጨንቀናል!

ምን አስጨነቀን?? ...

ወደዚህች ምድር የመጣነው በእንግድነት መሆኑን ማወቅ አለብን። በማረፊያችን ያላረፍን መንገድ ላይ ያለን እንግዶች ነን፣ አገር አቋራጭ ተጓዦችና በሷ ላይ አላፊዎች ነን፣ በሷ ላይ የምናልፍ መንገደኞች እንጂ የሷ አካሎች አይደለንም። አባይ በጣና ላይ እንደሚያልፈው ሁሉ እናልፍባታለን። በመጨረሻም አባይም ጣናም ይጠፋሉ። እኛና ዱንያም አንቀርም። የሷ አካል ብንሆን እንኳ እሷም ጠፊ ናትና እኛም ጠፊ ነን። መንገደኛ መሆናችንን ስናውቅ የተጓዥን ባህሪ መላበስ ይኖርብናል። ተጓዥ መንገደኛ በባህሪው ጓዝ አያበዛም። ሸክሙ ቀለል ያለ ነው። ተከራይቶ የሚኖር ሰው የሚኖርበት ቤት ቤቱ እንዳልሆነ ያውቃልና በሰው ቤት ትላልቅና ቋሚ ነገሮችን አያከማችም። ዱንያ የቱን ያህል ዕድሜ ቢኖራትም ፈራሽ ናት። የገነባት ጌታ አንድ ቀን ያፈርሳታል፤ እሷም እንደሰው ልጆች ሁሉ የተወሰነላት ዕድሜ አላት። ስለዚህ በሐሩር ቀን አንድ የዛፍ ጥላ ሥር ያረፈ መንገደኛ የፀሐዩዋን መቀዝቀዝ ጠብቆ ጥላውን ትቶ

እንደሚሄደው ሁሉ እኛም ትተናት እንሄዳለን። እንደመጣን ሁሉ እንሄዳለን። በዚህች ምድር ላይ አንቀርም። አላፊዎች ነን፤ ቋሚ አይደለንም። አልፎ ሂያጅ የሆነ ሰው ደግሞ ስለሷ እምብዛም መጨነቅ አይገባውም። የሚጨነቅ ካለ በርግጥም ሞኝ ሰው ነው። ይህ ነው የዱንያ ምንነት።

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዱንያ አላህ (ሱ.ወ.) ዘንድ ምንም ዋጋ እንደሌላት ነግረውናል። የትንኝ ክንፍ ያህል ዋጋ እንኳ የላትም ብለዋል። ትመዘን ቢባል ምንም እትመዝንም ማለት ነው። ግና ዋጋ የላትም ሲባል ለምድራዊ ሕይወታችሁ አትሥሩ ማለት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። የዋጋዋን ያህል ብቻ ነው ለሷ መሰጠት ያለብን። አላህ በሷ ላይ ኖረን፣ እሱን አምልከን፣ ፈተናዎችን አልፈን ወደመጨረሻው ዘላለማዊው ዓለም እንድንሻገር ነው የፈጠረን።

አስቲ ምን አሳሰበን?? ...

ዱንያ እንዲህ ናት እንግዲህ። በሷ ላይ በምናሳልፈው አጭር ዕድሜ ነገራችንና መንገዳችን ሁሉ ቀድሞውኑ ተከትቧል። ገና ስንፈጠር ሥራችን፣ ሲሳያችን፣ የምድር ላይ ዕድሜያችንና የመሞቻ ቀናችን፣ የጀነት እንሁን የእሳት... ሁሉ ተጽፏል። ስለዚህ አየኖርን ያለነው ቀድሞውኑ በተሰመረልን መንገድ ነው ማለት ነው። ያ ሲባል ግና ራሳችንን ልቅ እና ባለቤት አልባ አድርገን በዋዛ ፈዛዛ እንደፈቀደ እንኑር ማለታችን አይደለም። በተቻለን መጠን ሁሉ በጎ ነገር ፍለጋ እና መልካም ሥራ ላይ ማተኮር ይኖርብናል።

ዕድላችንና ዕጣፈንታችን ሁሉ በአላህ (ሱ.ወ.) እጅ ነው። ሰዎች በኛ ላይ ማድረግ የሚችሉት ትልቁ ነገር አላህ የፃፈልንን/የፃፈብንን ነገር መፈፀም ብቻ ነው። ከዚያ ውጭ ምንም ጉልበትም፣ ኃይልም ሆነ ብቃት የላቸውም። አይጎዱንም አይጠቅሙንም። የነካን እና የሚነካን ሁሉ ሊነካን የሚችለው አላህ (ሱ.ወ.) እንዲነካን የፈቀደው ነገር ብቻ ነው። ለዚህም ነው ጠቃሚም ሆነ ጎጂ፤ ሰጪም ሆነ ነሺ የፈጠረን አምላክ አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ነው የምንለው። ለዚህም ነው መሥራት እንጂ መጨነቅ አይገባንም የምንለው።

አስቲ ምን አስጨነቀን?? ...

የሚያሳስበን የሲሳያችን ጉዳይ ከሆነ አሱም ከሁሉም ነገር ቀድሞ ተጽፏል። ሊነጥቀን፣ ሊያግደን እና ሊከለክለን ቢሞክር ማንም አይቻለውም። ለየግላችን በጀታችን

ተመድቦልናል። አሰርቃለሁ፣ አቆርጣለሁ፣ አነፍጋለሁ ቢል ማንም አይቻለውም። የተፃፈልን ሲሳይ ከኛ ጋር አለና ስላልፈለግን ገፍተን አንመልሰውም። ባንፈልገውም እሱ ራሱ ይፈልገናል። ሪዝቃችን እንደ ሞት ቀናችን ሁሉ የቤታችንን በር ያንኳኳል። ብንሸሸውም አሳዶ ይደርስብናል። ስለተሰገበገብን ጎትጉን አናመጣውም። እንሸከም ብንል ተሸክመነው አንዞርም። የፈጠረን አላህ ሊለግሰን ቃል ገብቷል። የሚያስፈልገንን ሁሉ ሊያሟላልን እና ከርሣችንን ሊሞላ ፈቅዷል። የትም ብንሄድ ሪዝቃችን ራሱ ይከተለናል። ሞት እንደሚፈልገን ሁሉ እኛን ፍለጋ ያለንበት ድረስ ይመጣል። ስለዚህ ለምን ሃሳብ እናበዛለን?

ምን አሳሰበን?

ኮሚያሳድደን ጠላት ይኖርብን ይሆን?... ዕድሜያችን በአላህ (ሱ.ወ.) እጅ ነው። የወደደን የእንዲትም ቀን ዕድሜ አይጨምርልንም። የጠላን ቅንጣት ታክል አይቀንስብንም። ዕድሜ ቀድሞ የተወሰነና የተቆረጠ ነገር ነው። ያለ ቀናችን የምንሞት አይደለንም። ከሞት ቀናችን አንቀድምም፣ አንዘገይም። በሽታ፣ ሰዎችም ሆኑ ሌሎች አደጋዎች ምክንያት ናቸው እንጂ በሕይወታችን ወሳኞች አይደሉም። ቀናችን ሳይደርስ አይገድሉንም። ስለዚህ ምንም ሊያስፈራን አይገባም። በልጅነት በእናታችን ማኅፀን ውስጥ የጠበቀን አላህ ሁሌም ይጠብቀናል።

ጠላት ከሆነ ሁሉም አለው። ሰው ሆኖ የሚጠላው የሌለው ሰው የለም። መላእክትን ሳይቀር ሸይጣኖች ይጠሏቸዋል። ምርጦቹ የአላህ ነቢያትም፣ ደጋጎቹ የአላህ (ሱ.ወ.) ባሮችም ጠላት ነበራቸው። ፈርዐውን የነቢ ሙሳ ዋና ጠላት ነበር። ነቢ ዒሳ ለግድያ ተፈልገዋል። ቁረይሾች ነቢያችንን ሲያሳድዱ ነው የኖሩት።

እስቲ ምን ያሳስብናል? ....

የምድር ላይ ፈተና ለማንም አልቀረም። ለአላህ ቅርብ የሆኑ ባሮቹ ጭምር ተፈትነዋል። አባታችን አደም በሸይጣን ተፈተነዋል። ነቢዩ አዩብ በበሽታ ተፈትነዋል። ነቢዩ ዘከርያ በልጅ እጦት ተፈትነዋል። ነቢዩ የዕቁብ በልጆቻቸው ጥመትና በጠፋ ልጃቸው በነቢዩ ዩሱፍ ናፍቆት ተፈተነዋል። ነቢዩ ኑሕ በሕዝባቸው ተቀባይነት አጥተው ለበርካታ ዓመታት ጮኸዋል። ነቢዩ መሳ በፈርዐውን ጦር ተሳደዋል። ነቢዩ መሐመድን ቁረይሾች ተከታትለው ሊያጠፏቸው ሞክረዋል፤ የቲም ሆነው ከማደግ ጀምሮ እስከ ልጆቻቸው ሞት ሁሉን ፈተና ቀምሰዋል።

ምን ያሳስበናል? ..

ባልሠራነው ሥራ ሥማችን ጠፍቶ፣ ባልዋልንበት ውሎ ከብራችንም ተነከቶ ከሆነ ከኛ የሚበልጡ በርካታ ደጋግ የአላህ ባሮች ኖረውበታል፤ አልፈውበታል። ሰዎች የፈጠራቸውን አምላከ አላህን (ሱ.ወ.) ጭምር ሳይፈሩና ሳያፍሩ ወንጅለውታል፤ ሚስት አለው፣ ልጅ አለው፣ ወልዷል፣ ተወልዷል፣ ንፉግ ነው እጁ አይፈታም.. ብለው፣ በሌለው ባህሪ አነውረውታል። ያውም እያበላቸው እያጠጣቸው ነው እንዲህ የሚያደርጉት። በንፁህ ከባቢ ያደገችዋን ንጽህት መርየምን ንፅህናዋን እያወቁ ያለ ጋብቻ ዲቃላ ወለድሽ ብለው ሥሟን አጥፍተዋል። መናፍቃን የነቢያችንን ባለቤት እናታችንን እመት ዓኢሻን በዝሙት አነውረው የሷንም የተከበሩ ባለቤታቸውንም ከብር ነክተዋል። ነቢያችንን ነቢይነታቸውን እያወቁ ዕብድ፣ ድግምተኛ ብለዋቸዋል። ብንነወር፣ ብንታማ፣ ከኛ የበለጡ ፃድቃን ሁሉ ተነውረዋል፣ ታምተዋልና ምን ያሳስበናል!! ዋናውና ከኛ የሚፈለገው ቁምነገር እውነተኛ መሆንና በዓላማ መጽናት ነው። ሰዎች በሌለን ሥምና ግብር ይከሱናል። እውነተኞች ከሆንን በነውረኞች ትችት መደንገጥም ሆነ ወደኋላ መመለስ የለብንም።

እስቲ ምን ያሳስበናል ?!

በሽታ ከሆነ እሱም የሕይወታችን አንዱ አካል ነው። አላህ ነው የፈጠረው። ለፈተና ነው የፈጠረው። አላህ (ሱ.ወ.) በሽታን እንደፈጠረው ሁሉ ጤናንም ፈጥሯል። መታመም እንዳለ ሁሉ መዳንም ይኖራል። ለሁሉም ዓይነት በሽታ አላህ (ሱ.ወ.) መድኃኒትን አስቀምጧል። በሽታ ከበሽታነቱ ባለፈ ፋይዳም እንዳለው ማወቅ ይኖርብናል። ወንጀላችን ለማርገፍ ሰበብ ነው። ወደ አላህ ፊታችንን እንድንመልስም ምክንያት ነው። እኛስ ማን ስለሆንን ነው የማንታመመው! ... ነቢያችንም ሆነ ሌሎች ነቢያት ሁሉ ታመዋል። ነቢዩ አዩብ (ዐ.ሰ.) ከ18 ዓመት በላይ እንደታመሙ ነው የሚነገረው። ብቻ አላህ ከልባችን መታመምና መቆሸሸ ይጠብቀን። ንፁህ ቀልብም ይስጠን። አካላዊ በሽታ ቀላል ነው። ኢንሻአላህ የሚድን ነው።

ምን ያስጨንቀናል? ...

ምቀኛ የሌለው ማን አለ!። በየሥራ ቦታችንና በሠፈር ጎረቤታችን ሞልቷል። አላህ ለሚቀልበን እሱ የሚጨንቀው ብዙ ነው። አላህ ለሠጠን እሱ የሚቃጠል የትየሌለ ነው። በመኖራችንና በመተንፈሳችን ምድር ላይ ሲያየን የሚከብደው በርካታ ነው።

ከቤት ጀምሮ እስከ ሥራ ቦታችን ድረስ የቀሉ ዐይኖችና የተቃጠሉ ልቦች ሊሸኙን ይችላሉ። በመልካችን፣ በቁመናችን፣ በዕውቀታችን፣ በሥልጣናችን፣ በሃብታችን፣ በሰው ዘንድ ባለን ተወዳጅነት፣ በትዳራችን፣ በምንለብሰው ልብስ፣ በምንበላው ምግብ፣ አላህ በለገሠን ልጆች፣ በሠራነው ቤት፣ በምንነዳው መኪና... የሚቀኑ የሚመቀኙ አሉ። ምቀኛ በገዛ እጁ ራሱን የሚረብሽ ነው። ውሰጡ ሰላም የለውም። ውስጡ የሚነድ እሳት ነው። ያንን እሣት ወደኛ ማጋባት ነው የሚፈልገው። አላህ የሰጠን ችሮታ ነው የሚያቃጥለው። እንዴት አገኘ፣ እንዴት በለጠኝ፣ እንዴት አለፈለት፣ እንዴት አማረበት... እንዴት... እንዴት... የዘወትር ጥያቄው ነው። እኛ የሠጠንን አላህን ስለፀጋው እናያለን፤ ምቀኛ ደግሞ የፀጋውን ባለቤት ትቶ እኛን ያያል። ምቀኛ የሌሎች ጥገኛ ነው። እኛ የራሳችንን ሕይወት እንኖራለን፤ እሱ ግን የራሱን ትቶ የኛን ሕይወት ይኖራል። ከራሱ በላይ የኛ ሕይወት ያሳስበዋል። ከራሱ ማግኘት በላይ የኛ ማጣት ያስደስተዋል። በየዘመኑ የዚህ ዓይነት ሰዎች አሉ። የኛን እንጂ የራሳቸውን ሕይወት አይኖሩም። ለምቀኛ ትኩረትም ሆነ ቦታ መስጠት የለብንም። ከሱ መራቅ፣ መናቅ፣ መደበቅና ከከፋቱ በአላህ መጥጠበቅ ነው የሚሰፈልገው። "ወሚን ሸርሪ ሓሲዲን ኢዛ ሐሰድ"። አላህ የልቡን እሣት ያብርድለት።

ኢታስብ ወዳጄ ...

መብበደልህ ያሳስብህ ይሆናል፤ ያለአግባብ የተሠራብህ ግፍ አንገብግቦህ ይሆናል። አይዞህ አትዘን። ብቻ አንተ በዳይ አትሁን። ግና ሰው ሆኖ በደል ያልደረሰበት ማን አለ!። ያላግባብ ያልተገፋ ማን አለ!። አላህን በማይፈራ ሰው ንብረቱን ያልተቀማ፣ በውሸት ወሬ ሥሙ ያልጠፋ፣ ያልተሰደበ፣ ያልተናቀ ... ማን አለ!። እኛ ሙስሊሞች በመጨረሻው ዓለም ስናምን የካሳ እና የጀዛ ቀን መሆኑንም እናምናለን። ሌላው ቀርቶ ቀንድ የሌላት ላም በቀንዳም ላም በደረሰባት በደል ትካሳለች። በዳይ ሰው በዳይ እንደሆነ ውስጡ ይነግረዋል። ህሊናውም ሰላም ይነሳዋል። በዚህም ሆነ በመጨረሻው ዓለም ዕረፍት የለውም።

የጊዜ ጉዳይ እንጂ በዚህ ምድር ላይ የእጁን ያገኛል። ዛሬ ቢፈነድቅ ቢደሠት ለጊዜው ነው። ዛሬን ቢያልፍ ነገ ሌላ ኬላ አለበት። በትንሳኤ ቀን የሚጠበቀው መዓት ከባድ ነው። በቂያማ ቀን ለምርመራ ዋናው መርማሪ ፊት ይቆማል። መልካም ምንዳውን ሁሉ ዐይኑ እያየ ይነጠቃል። የበደላቸውን ሰዎች እንዲከስ ይደረጋል። የሚከሰውም ዱንያ ላይ ከሠራው የመልካም ሥራ ምንዳው እየተወሰደ ነው። ዐይን እያየ የራስን መልካም ሥራ አሳልፎ ከመስጠት በላይ ምን ህመም አለ!!። በዚህ መልኩ የበደለውን

ሁሉ ይከሳል፤ የሰረቀውን ሁሉ ሳይወድ በግዱ ይመልሳል። መልካም ሥራ ከሌለው ወይም ለተበዳዮች ተሠጥቶ ካለቀ፣ ከተበዳይ መጥፎ ሥራ ተቀንሶ ዕዳ እንዲሸከም ይደረጋል።

በደል የትንሳኤ ቀን ድርብርብ ጨለማ ነው። በዳይ ሰው ኪሳራው ብዙ ነው። ማረፊያውም ጨለማ ነው። ለበዳይ ሰው አዘንለት እንጂ ተበደልኩ ብለህ አትማረር። የተበዳይ ዱዓ ምላሽ አለው። የተበዳይን ጉዳይ አላህ አይረሳም። አንድ ቀን ይመልስለታል። እንባውን በማረ ሁኔታ ያብስለታል። በደል ጉዳት ቢመስልም ትርፍ አለው። እናም ምን አሳሰበህ...

ምን ያሳስበናል...

በምንወደው ሰው ተከድተን ሊሆን ይችላል፤ የምንቀርበውና የምናምነው ሰው ጎድቶን ይሆናል። እርግጥ ነው ከሚቀርቡን ሰዎች በኩል የሚደርሰው ጉዳት ያማል። ርቀቱም ቅርበት ስላለው ነው መሰል ውጋቱም ጥልቅ እና ከባድ ነው የሚሆነው። ይህ የሆነው ለሰዎች የሰጠነው ዋጋ ከፍ ያለ በመሆኑ ነው። ራሳችንን ጥለን ከአላህ በላይ ኡነርሱን አምነን ስለተደገፍንባቸው ህመሙ ከበደን፤ በቀላሉም ወደቅን። የዱንያ ቀናት ምን ይዘው እንደሚመጡ አይታወቁም። ሰዎች የሆነ ቀን ሊለወጡ፤ ሀሳባቸውንም ሊቀይሩ እንደሚችሉ እንወቅ። ስለሆነም ፍፁም በሆነ መልኩ በሰው ልጆች አንተማመን። የቁርጥ ቀን ወዳጆቼ ናቸው ብለንም ፍፁም በሆነ መልኩ ሰዎችን አንመን። ሳናስበው አንድ ቀን ያሳፍሩናል። ዛሬ ላይ ሰው ለሰው የሐዘን ምንጭ ሆኗል። ከወዲህ ወዲያ ሐሜትን የሚያመጡ፤ በምቀኝነት የተበከሉ፤ በውሸት የተነገሩ ሆነዋል። በአሉ አሉ ይኖራሉ። በገንዘብ ጉዳይ የሚካካዱ ብዙ ናቸው። በጥቅም የሚጣሉ በርካቶች ናቸው። ከሰው የሰውን ልጅ ብቻ እንጠብቅ። ከሩቅም ሆነ ከቅርብ ሰው በሚደርስብን ጉዳት አንገረም።